# ጥናት አንድ አስቴር 1፡1-22 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በዚህ በአንድ ምዕራፍ ውስጥ ተደርገው የምናገኛቸው ሶስት ግብዣዎች ሲኖሩ፤ ከእነዚህም ሁለቱ በንጉሱ በጠረክሲስ የተደረጉ ሲሆን፤ የቀረው አንደኛው ደግሞ በሚስቱ በንግሥት አስጢን የተደረገ ነበረ። እነዚህም አንደኛው በቁ3 ላይ "ለመኳንንቱና ለሹማምቱ" ያደረገው፤ ሁለተኛው በቁ5 ላይ "በሱሳ ግንብ ለነበሩት፣ ከትንሽ እስከ ትልቅ ላለው ሕዝብ ሁሉ" ያደረገው ሲሆን፤ ሶስተኛው ደግሞ በቁ9 ላይ "ንግሥት አስጢንም በንጉሥ ጠረክሲስ ቤተ መንግሥት እንደዚሁ ለሴቶች ግብዣ አድርጋ ነበር" በማለት የተነገረው ነው።
2. በቁ4 እና ቁ5 ላይ ትልቅ ግብዣ እንደነበረ የተነገረ ሲሆን፤ በተጨማሪ ደግሞ ቁ6-8ትን ስናይ እያንዳንዱ ነገር ቀለሙን እንኳን ሳይቀር በጥንቃቄ የተዘጋጀ መሆኑና ሰውም ደስ ያሰኘውን ያህል መጠጣት መቻሉ ትልቅነቱን ያረጋግጥልናል። ንጉስ ጠረክሲስ ይህንን ያህል ከፍተኛ ወጪና ትልቅ ዝግጅት የሚጠይቀውን ግብዣ ለማድረግ ስለተነሳሳበት ምክንያት ከክፍሉ የምንረዳው በተለይም ቁ4 "ለእነርሱም የመንግሥቱን ሰፊ ሀብት፣ የግርማውን ታላቅነትና ክብር አንድ መቶ ሰማንያ ቀን ሙሉ አሳያቸው" በማለት ይነግረናል።
3. ንጉሱ ለሕዝቡ ባካሄደው ትልቅና አስገራሚ የድግስ ዝግጅት በተጨማሪ የታደመውን ሕዝብ ለማስገረም የፈለገበት የመጨረሻው መንገድ መልከ መልካም የሆነችውን ሚስቱን ውበቷን በማሳየት ታዳሚውን ሊያስገርም ነገረ። ይህ የመጨረሻና ማሳረጊያ አድርጎ ሊጠቀምበት የፈለገው ንግሥት አስጢንን ማስመጣት እንደሌላው ቀላል አልሆነለትም፤ ምክንያቱም አስጢን እንድትመጣ ሲጠይቃት ለመምጣት ፈቃደኛ ባለመሆኗ ነው።
4. ምንም እንኳን ንጉሱ ጠረክሲስ በቁ10 ላይ እንደምናነበው "በሰባተኛው ቀን ንጉሥ ጠረክሲስ ከወይን ጠጁ የተነሣ ደስ ስለ ተሰኘ" የሚለው አነጋገር ከጠጣው የወይን ጠጅ የተነሳ ሞቅታ ውስጥ ገብቶ እንደነበረ የሚጠቁመን ነው። የንግስቲትም ንጉሱን በዚያን ዓይነት ድግስ ውስጥ ንጉስ ሲጠራት እንቢ ለማለት የድፍረት ድፍረት ማግኘቷ የእግዚአብሄር እጅ ያለበት እንደሆነ ብንረዳም እንኳን፤ ባደረገችው ግብዣ ላይ እርሷም እንደ ባሏ የመጠጥ ግፊት ሊሆን እንደሚችል መገመት ስህተት አይሆንም።
5. እነዚህ ሊቃውንት ንጉስ ጠረክሲስ ንግሥት አስጢንን አስመልክቶ ለጠየቃቸው ጥያቄ የሰጧቸው ሁለት ነገሮች ሲሆኑ፤ አንደኛው  አስጢን ወደ ንጉሡ ወደ ጠረክሲስ ዘንድ ከእንግዲህ ወዲህ ፈጽሞ እንዳትገባ፤ ሁለተኛው ደግሞ የእቴጌነቷ ክብር ከእርሷ ለምትሻል ለሌላዋ እንዲሰጥ የሚሉ ናቸው።
6. ምንም እንኳን በዚህ መጽሐፍ ምዕራፍ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ መጽሐፉ ውስጥ እግዚአብሄር የሚል ነገር ባይነበብም፤ እነዚህ ሁሉ የተለያዩ ነገሮች አንዱ ከሌላው ጋራ ባልተዛባ መልኩ ተሰካክተው ስመለከት፤ በተለይም ዛሬ እንደታሪክ ሰፍሮልን ስናነበው፤ እግዚአብሄር ራሱ አንድ በአንድ ነገሮችን እያቀነባበረ እንደነበረና ለዚህም አሰራሩ በእርሱ በሚያምን ሰው ሳይሆን የራሱን ክብርና ዝና ለሰዎች ለማሳየት ጥማት ባደረበት ንጉሥ አማካኝነት ማከናወኑ የእርሱን እጅ በግልጽ ያሳየኛል።

# ጥናት ሁለት አስቴር 2፡1-23 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ለንጉሱ ቆንጆ ቆንጆ ልጃገረዶች እንዲፈለጉ፣ ሁሉም ልጃገረዶች በጃንደረባው በሄጌ ሃላፊነት ሥር በመሆን ለውበት የሚያስፈልገው እንክብካቤ ሁሉ እንዲደረግላቸው ተደርጎ፤ በመጨረሻም ንጉስ ጠረክሲስን ደስ የምታሰኘው ልጃገረድ በቀድሞ ሚስቱ በአስጢን ፈንታ ንግስት እንድትሆን የሚል ምክር ነበረ።
2. መርዶኪዎስ ከብንያም ነገድ ነበረ፣ አባቱ ኢያዕር፣ አያቱ ሰሜኢና ቅድም አያቱ ደግሞ ቂስ ቂስ ይባላሉ፤ መርዶኪዎስ ይኖር የነበረው የሱሳ ግንብ በተባለው ሥፍራ ሲሆን፤ እርሱ የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ከማረካቸው ከይሁዳ ንጉሥ ከኢኮንያን ጋራ በምርኮ ከተወሰዱት መሃል አንዱ ነበር። ይህንን ሰው ከሳዖል ጋራ የሚያመሳስሉት ነገሮች አንዱ ከብንያም ነገድ መሆኑ ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ ቂስ ከሚባለው ሰው የዘር ግንድ መሆኑ ነው።
3. አስቴር ከመባሏ በፊት የመጠሪያ ስሟ የነበረው ሃደሳ የሚል እንደነበረ እናያለን። በአስቴርና በመርዶኪዮስ መሃል የነበረው ግንኙነት እርሷ ለእርሱ የአጎቱ ልጅ ነበረች። አባትና እናቷን ካጣች በኋላ ደግሞ መርዶኪዎስ አስቴርን ወስዶ እንደ ራሱ ልጅ በማድረግ እንደ አባት ሆኖ እንዳሳደጋት እናነባለን። ከአስተዳደጓ ውጭ ስለ አስቴር ከቁጥር ሰባት ማየት የምንችለው፣ በሰውነቷም ሆነ በመልኳ ውብ እንደነበረችም ይነግረናል።
4. አስቴር በልጅነቷ አባቷንና እናቷን እንዳጣች ከቁ7 እንረዳለን፤ ስለዚህም እግዚአብሄር በቸርነቱ መርዶክዮስን ባያዘጋጅላት ኖሮ እንኳንስ ያንን የሚያህል ትልቅ ግዛት ንግሥት ለመሆን ይቅርና ሕይወትን በቅጡ መኖር የምትችልበት ሁኔታ ምን ያህል ሊከብድ እንደሚችል ለማንም ግልጽ ነው። ሁለተኛውን ጥያቄ ለመመለስ እያንዳንዱ የራሱን ሃሳብ በመስጠት ይሳተፍ።
5. አስቴር ሰውየውን ደስ አሰኘችው፣ በሄጌ ዘንድ መወደድን አገኘች፣ ምንም ሳይቆይ ወዲያውኑ የውበት መንከባከቢያዋንና የተለየ ምግብ ሰጣት፣ ከቤተ መንግሥቱ የተመረጡ ሰባት ደንገጡሮች መደበላት፣ እርሷንና ደንገጡሮቿን ምርጥ ወደ ሆነው የሴቶች መጠበቂያ አዛወራቸው።
6. በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ስለ አስቴር ባህርይ የሚታየኝ ነገር ቢኖር፤ ምሥጢር ጠባቂ ወይም ቃሏን የምትጠብቅ ሴት እንደሆነች ነው የማየው። ቁ12 እንደሚነግረን አንዲት ሴት እንኳን ወደ እርሱ ለመግባት የአንድ አመት ጊዜ ሥለሚፈጅ ቢያንስ ዓመት ይፈጅበታል ማለት ነው።
7. አስቴር ልጅ ሳለች ለመርዶኪዎስ መታዘዝ ብቻ ሳይሆን ንግሥት ሆናም ትዕዛዙን እያከበረች እንደሆነ ቁ20 ይነግረናል። በጠባቂው በሄጌ ፊት ሞገስ አግኝታለች (ቁ9)፣ በሚያዩዋት ሁሉ ዘንድ ሞገስ አገኘች (ቁ15)፣ በንጉሱ በጠረክሲስ ፊትም ሞገስና መወደድን አግኝታለች (ቁ17)።
8. ከዚህች ሴት ህይወት ለራሳችን መማር የምንችለው ነገር ቢኖር እግዚአብሄር አምላክ አንድን ነገር በእጃችን ሊያስገባ ሲፈልግ፤ እኛ ለራሳችን የምናደርጋቸውም ነገሮች ሆኑ ሰዎች ለእኛ የሚያደርጉልን ነገሮች ሳይሆኑ ከእርሱ ዘንድ ሞገስን ማግኘት ብቻ በቂ ሊሆነን እንደሚችል በግልጽ ያስተምረናል።

# ጥናት ሶስት አስቴር 3፡1-15 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ንጉሱ ሐማን ከፍ ከፍ አደረገው፣ ከሌሎቹ መኳንንት ሁሉ በላይ ከፍተኛውን ሥልጣን በመስጠት አከበረው፣ ሹማምንቱ ሁሉ ለሐማ ተንበርክከው እጅ በመንሳት አክብሮታቸውን እንዲገልጡለት ንጉሥ ትዕዛዝ ሰጠ፣ መርዶኪዮስ ወድቆ አልሰገደም፣ አክብሮትም አላሳየውም።
2. በትንቢተ ዳንኤል ውስጥ ንጉሱ ናቡከደነጾር ሃውልት አሰርቶ ሕዝቡ ሁሉ እንዲሰግድለት ትዕዛዝ ባስተላለፈበት ወቅት ሶስቱ አይሁዳውያን ወጣቶች እርሱ ላቆመው ሃውልት በምንም ዓይነት እንደማይሰግዱ ውሳኔአቸውን ያስተላለፉበት ሁኔታ ከዚህ ሁኔታ ጋራ ይመሳሰላል።
3. በ2፡10-11 ባለው ክፍል ውስጥ ስናነብ መርዶኪዎስ ለአስቴር የማን ወገን እንደሆነችና ከየት አገር እንደመጣች እንዳትናገር አዟት እንደነበረ እንደነበረ ሲሆን፤ በ3፡3-4 ውስጥ ደግሞ የምናየው እርሱ ራሱ ግን ለንጉሱ አገልጋዮች አይሁዳዊ መሆኑን ነግሯቸው እንደነበረ ስናይ በሁለቱ መሃል የሃሳብ ክፍተት መኖሩን ማስተዋል ይቻላል።
4. በቁ4 መሰረት ይህ ጥያቄ ከሰዎቹ ዘንድ ይቀርብለት የነበረ አንድ ወይም ሁለት ቀን ብቻ ሳይሆን በየእለቱ የሚቀርብለት እንደነበረ እናነባለን። አንድን ጥያቄ ሰው አንድ ጊዜ ብቻ ቢጠየቅ የመጣ ይምጣ በማለት አደርጋለሁ ወይም አላደርግም በማለት መገላገል ይችላል፤ ጥያቄው ግን በተደጋጋሚና በየቀኑ ሲሆን ሃሳብን ለመቀየር ሰፊ እድል ስለሚሰጥና ፍርሃትም ሊጨምር ስለሚችል የመርዶኪዮስን ፈተና ያከብደዋል እላለሁ።
5. ዮሴፍ በንጉሱ ዘንድ ሞገስ ማግኘቱንና ከፍ ከፍ መደረጉን የተጠቀመው የራሱን ትልቅነት ለማወጅና ለማረጋገጥ ሳይሆን የሕዝብን ሕይወት ለማዳን ሲሆን፤ በአንጻሩ ሐማ ደግሞ ከፍታውን የተጠቀመበት የራሱን ክብር ለማስጠበቅና ሕዝብን ከምድረ ገጽ ለማጥፋት እንደነበረ ነው ለእኔ የሚታየኝ።
6. በአገሪቱ ውስጥ የሚገኙትን አይሁድ ሁሉ ወደ መግደል ሃሳብ የደረሰበት ዋነኛው ምክንያት ሆኖ የተጻፈው መርዶኪዎስ አይሁዳዊ መሆኑን ባወቀ ጊዜ አንድ እርሱን ብቻ መግደል በጣም ትንሽ ነገር አድርጎ ስለቆጠረው ነው።
7. ስለ ሐማ ባህርይ የሚነግረኝ እርሱ የፈለገውን ለማስፈጸም ለመዋሸት ወደ ኋላ የማይል፣ ደግሞም የሰዎች መከራና ሥቃይ የእርሱ ደስታው እንደሆነ አያለሁ። ስለ ንጉሱ ባህርይ የማየው ደግሞ “ሕዝቡንም እንዳሻህ አድርገው” በማለት አሳልፎ መስጠቱ ለሚያስተዳድረው ሕዝብ ግድ እንደሌለው፣ ሌላው የሰማውን ነገር እውነተኛነት ሳያረጋግጥ ፍርድ የሚሰጥ ችኩል ሰው መሆኑን ተመልክቻለሁ።
8. እግዚአብሄር አምላክ ሕዝቡን እስራኤልን ከእርሱ በስተቀር ለሌላ ለማንም መስገድ እንደማይኖርበት በዘጸ 20 ላይ ግልጽ አድርጎ ተናግሯል። መርዶኪዮስ የእግዚአብሄርን ሕግ ለመከተል የወሰነና የጨከነ አይሁዳዊ በመሆኑ ምንም እንኳን ትዕዛዙ ከንጉሥ የመነጨ ቢሆንም ከአምላኩ ትዕዛዝ አስበልጦ የንጉሥን ትዕዛዝ ስለማይቀበል ነው በድፍረት በእንቢተኛነቱ መጽናት የፈለገው።

# ጥናት ሶስት አስቴር 4፡1-17 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ከንጉሱ የወጣውን ትዕዛዝ መርዶኪዎስ ባወቀ ጊዜ ያደረጋቸው ነገሮች፤ ልብሱን መቅደድ፣ ማቅ ለብሶና በራሱ ላይ ዓመድ መነስነስ፣ ድምጹን ከፍ በማድረግ አምርሮ በመጮህ ወደ ከተማይቱ መካከል በመውጣት ነበረ ትዕዛዙን ያስተናገደው። ጸሐፊው በቁ2 ላይ እንደሚነግረን ማቅ የለበሰ ሰው ወደ ቤተ መንግሥት መግባት የተከለከለ ስለሆነ ነው።
2. ይህ አዲስ የወጣው ንጉሳዊ ዓዋጅ በግዛቱ ሁሉ ላይ ያሉትን አይሁድ ሁሉ ከማስደንገጡ የተነሳ ሁሉም በሃዘን እንደተሞሉ፣ ጾም እንደጀመሩ፣ እንዳለቀሱ፣ እንደጮሁና፣ ብዙዎቹ ደግሞ መኝታቸውን በማቅና በዓመድ ላይ አድርገው እንደነበረ ጸሐፊው ይነግረናል።
3. የመርዶኪዎስን ሁኔታ ከሰዎቿ በሰማች ጊዜ የወሰደቻቸው እርምጃዎች ሁለት እንደነበሩ ነው የማየው፤ የመጀመሪያው ነገሩ እንዳሳዘናት ስሜቷን መግለጥ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በማቁ ፈንታ የሚለብሰው ልብስ መላክ ነበረ። ለመርዶኪዎስ ሐዘኗ ብቻ ወይም ደግሞ የተላከለት ልብስ ለእርሱ የሚፈልጋቸው አይነት መልሶች ሆነው አልተገኙም።
4. ሃታክ ለአስቴር እንዲያደርስ ከመርዶኪዎስ የተሰጡት መረጃዎች፤ መርዶኪዎስ የደረሰበትን ነገር ሁሉ፣ ሃማ በንጉሥ ግምጃ ቤት ያስገባው ገንዘብ መጠን፣ የወጣውን የአዋጁን ቅጂ ሲሆን፤ በተጨማሪም ወደ ንጉሱ ገብታ ስለሕዝቡ ምህረት እንድትማልድ ላከባት።
5. አስቴር በሃታክ በኩል የአይሁድን ዘር ሁሉ በመወከል ወደ ንጉሱ እንድትገባ ከመርዶኪዎስ ለቀረበላት ሃሳብ በጭራሽ ሊደረግ የማይችል ነገር እንደሆነ አድርጋ ምላሽ እንድትሰጥ ያደረጋት አንድ ነገር ቢኖር ቁ11 እንደሚነግረን ወደ ንጉስ ሣይጠሩ መግባት ሞት እንደሚያስከትል ስለሚናገር እርሷንም ይህንን እንዳታደርግ ያደረጋት የሞት ፍርሃት መሆኑን እናያለን።
6. መርዶኪዎስ የሰጣት አራት ሃሳቦች 1ኛ) በንጉስ ቤት በመሆኗ እንደማትድን ማስረዳት፤ 2ኛ) እሷ ባታደርገው ለአይሁድ ደህንነት ከሌላ ሥፍራ እንደሚመጣላቸው መንገር፤ 3ኛ) ለአይሁድ ከሌላ ሥፍራ ደህንነት ሲመጣ እሷና የአባቷ ቤት ግን እንደሚጠፉ ማስረዳት፤ 4ኛ) ወደ ንግስትነት የመጣችበት ለዚህ ጊዜ ሊሆን እንደሚችል መንገር ነበሩ።
7. በዚህኛው መልዕክቷ ያለቻቸው ነገሮች በሱሳ ያሉትን አይሁድ ሁሉ እንዲሰበስብ፣ ስለ እርሷ እንዲጾሙ፣ ቀንም ሆነ ሌሊት እንዳይበሉና እንዳይጠጡ የሚል ሃሳብ ላከችለት። አስቴር ህጋዊ እንዳልሆነ ብታውቅም ወደ ንጉሱ ለመግባትና ሕይወቷንም ቢያስከፍላት ለመክፈል ፈፍቃደኛ እስከመሆን ደርሳለች።
8. ለመርዶኪዮስ ወይም ደግሞ በአካባቢው ለሚገኙት የአገሩ ሰዎች ብቻ ሳይሆን በንጉሱ ግዛት ውስጥ ለሚገኙት አይሁዶች ሁሉ የሞትና የሽረት ጊዜ መሆኑን በደንብ ስለተረዳ ቆራጥነት በተሞላው አነጋገር ለአስቴር መልስ በመስጠቱ ምክንያት እግዚአብሄር አምላክ የአይሁድን ሞት ለመሻር ብቻ ሳይሆን የአይሁድ ጠላት የሆነውን ሐማንም ለመበቀል ምክንያት አድርጎ ይህንን ሰው ሲጠቀምበት እናያለን።

# ጥናት አምስት አስቴር 5፡1-14 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ምንም እንኳን እርሷ ራሷና ሌሎችም ብዙዎች ወደ አምላኳ እንደጸለዩ ብታውቅም እንኳን እንደ ሰው ወሰደች ከምላቸው ጥንቃቄዎች የመጀመሪያው ከክብሯ ያልተገባ ተራ ልብስ ለብሳ ሳይሆን ንጉሱን የሚመጥን የክብር ልብሷን መልበሷ፣ ሁለተኛው ደግሞ ሕጉን በተከተለ መንገድ ንጉሱ የወርቅ ዘንጉን እስኪዘረጋላት ድረስ ቆማ መጠበቋ ናቸው።
2. እግዚአብሄር ለንግሥቲቱ በንጉሱ ፊት ይህ ነው የማይባል ሞገስ እንደሰጣት የሚነግሩን ሃሳቦች፤ በቁ2 ላይ የምናነበው እርሷን ሲያያት በእጁ የያዘውን የወርቅ ዘንግ መዘርጋቱ የመጀመሪያው ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ በቁ3 ላይ የምናነበው እስከ መንግሥቱ እኩሌታ እንኳን ቢሆን ሊሰጣት ፈቃደኛ መሆኑን መግለጹ የተቀበለችውን የሞገስ ትልቅነት ይነግሩናል።
3. ቁ9 ላይ እንደምናነበው ሐማ ወደ ንግሥት አስቴር ግብዣ ከንጉሱ ጋራ እንዲመጣ የተጋበዘው ሰው እርሱ ብቻ መሆኑን ሲያውቅ ልቡ በደስታ እንደተሞላና መንፈሱም እንደረካ ይነግረናል። ምንም እንኳን ሐማ በዚያ ሁኔታ በጣም ደስተኛ ቢሆንም ሌላ በነበረው ደስታ ላይ ውሃ ያፈሰሰበት ነገር እንደነበረ ይኸውም የመርዶክዮስ ለእርሱ አለመስገድ ቁጣው እንዲነድ እንዳደረገው እናነባለን።
4. በእነዚህ ሁለት ቁጥሮች ውስጥ እንደምናነበው ከሆነ ሐማ ሚስቱንና ወዳጆቹን የሰበሰበበትን ዋነኛ ዓላማ ጉራ ለመንዛት ነው ብንል በምንም መንገድ ከእውነት የራቅን አንሆንም።
5. ይህ ሰው እነዚህን ሰዎች ሰብስቦ ካነሳቸው ርዕሶች መሃል ጥቂቶቹ፤ ስለ ሐብቱ ታላቅነት፣ ስለ ልጆቹ ብዛት፣ ንጉሱ ምን ያህል እንዳከበረው፣ ከሌሎች መኳንንትና ሹማምንት በላይ እንዴት ከፍ ከፍ እንዳደረገው የሚሉት ይገኙበታል።
6. የሐማን ልብ ያስፈነደቀውንና በብዙ ጉራ እንዲናገር ያበቃውን ከንጉሥ ጠረክሲስ ዘንድ ያገኘውን ሞገሥ በመልካም እንዳያጣጥመው የሐዘን ደመና ያጠላበት ነገር የመርዶኪዎስ ለእርሱ ወድቆ አለመስገድና ሌሎች የሰጡትን አይነት መንቀጥቀጥ አለማሳየቱ እንደሆነ ቁ13 ገልጾ ይነግረናል።
7. በቁ14 ላይ በመፍትሄነት የተሰጠው ሃሳብ ቁመቱ አምሳ ክንድ የሆነ መስቀያ እንዲያስተክልና መርዶክዮስ እንዲሰቀልበት በጠዋት ለንጉሡ እንዲነግረው የሚል ሲሆን ይህም ሃሳብ ሐማን በጣም ደስ እንዳሰኘው እናነባለን።
8. ንግሥቲቱ እርሱን ብቻ ከንጉሱ ጋራ ተጋባዥ አድርጋ መጥራቷ ለልቡ መኩራራትና የጉራ መንዣው ምክንያት አድርጎ ሲጠቀምበት ነው የምናየው። እግዚአብሄር ይህንን ሰው ለማዋረድ ይህንን ዓይነት አሰራር መጠቀሙ ምንም እንኳን ጠላት ያሸነፈና እግዚአብሄር የተሸነፈ በሚመስልበት ወቅት በትዕግሥት እርሱን መጠበቅ እንደሚኖርብን ያስተምረናል።

# ጥናት ስድስት አስቴር 6፡1-14 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ጸሐፊው በዚህ ሥፍራ “በዚያች ሌሊት” ብሎ የተናገረላትን ሌሊት ለማየት ምዕራፍ 5 የመጨረሻዎቹን ቁጥሮች ስናይ የሐማ ሚስትና ወዳጆቹ ለመርዶኪዎስ ሞት በዶለቱበት ምሽት እንደሆነ እናነባለን። ንጉሱ ናቡከደነጾርና ንጉሱ ዳርዮስ እንቅልፍ ባጡ ጊዜ ሁለቱም እንቅልፍ የሚያሳጣ ምክንያት ነበራቸው፤ የዚህን ንጉስ እንቅልፍ ማጣት ከሁለቱ የሚለየው ነገር ቢኖር ለእንቅልፍ ማጣቱ ምንም ዓይነት እንቅልፍ ሊነሳው የሚችል ምክንያት እንደነበረ ምንባቡ የሚነግርን ነገር ያለመኖሩ ልዩ ያደርገዋል።
2. የእግዚአብሄር ቅንብር እንደሆነ የሚጠቁሙኝ ሃሳቦች፤ በመጀመሪያ ደረጃ የንጉሱ እንቅልፍ ማጣት ለመርዶኪዮስ ስቅላት በተወሰነበት ቀን መሆኑ፣ ሌላው ደግሞ ሊያደርግ የሚችላቸው ሌሎች ነገሮች ሊኖሩ ሲችሉ የታሪክ መጽሐፍ ለመክፈት መነሳቱ፣ ሰስተኛ ደግሞ ከታሪክ ሁሉ መርዶኪዎስን የሚመለከት ታሪክ እንዲያነብ መሆኑ የእግዚአብሄር እጅ እንዳለበት ያሳየኛል።
3. መርዶኪዎስ ክብርንና ማዕረግን ለማግኘት ብሎ ሳይሆን መደረግ አለበት ብሎ ያመነውን ነገር በማድረግ የንጉሱን ሕይወት እንዳተረፈ ይታወቃል፤ ይህም ሆኖ ነገሮችን ሁሉ ከላይ ሆኖ የሚያይ ጌታ ለክብርና ለማዕረብ ብሎ ባያደርገውም እንኳን እግዚአብሄር ጊዜውን ጠብቆ እንዳከበረው ሁሉ፤ እኛም ዝም ብለን እግዚአብሄር ደስ የሚሰኝበትን ነገር ብቻ ስናደርግ እርሱ ጊዜውን ጠብቆ ከፍ ከፍ እንደሚያደርገን እንመን።
4. በእኔ አመለካከት ይህ አጋጣሚ ነው ብዬ አላምንም፤ እግዚአብሄር አቀነባበራቸው በማለት ከላይ ባሉት ቁጥሮች እንደዘረዘርናቸው ነጥቦች ሁሉ ይህም አንደኛው የመለኮት ቅንብር እንደሆነ እንጂ እንደ እድል የሆነ ነገር ነው ብዬ አላምንም።
5. “ንጉሱ ከእኔ ይልቅ የሚያከብረው ማን አለ?” በማለት ለራሱ በውስጡ ጥያቄ እንዳቀረበ ቁ6 ይነግረናል። ይህ የንጉስ ትዕዛዝ የሚደረግለት ሰው መርዶኪዎስ እንደሆነ ሐማ አስቀድሞ ቢያውቅ ኖሮ፤ እኔ እንደሚመስለኝ ለራሱ አስቦ ከተናገራቸው ነገሮች በብዙ እጥፍ ያነሰ ነገር ለንጉሥ እንደሚያቀርብ ምንም ጥርጥር የለኝም።
6. ይህ ሐማ የተባለ ሰው የመርዶኪዎስ ጠላት ብቻ ሳይሆን የአይሁድ ሁሉ ጠላት ሆኖ ሊያጠፋቸው የተነሳ ሰው እግዚአብሄር መልሶ በፊቱ ውርደት እንደተከናነበ ሁሉ፤ መዝሙረኛውም እግዚአብሄር ከፍ ከፍ ሲያደርግና በረከቱን ሲያፈስ ጠላቶች እያዩ እንደሆነ መናገሩ ሁለቱን ሃሳቦች አንድ ያደርጋቸዋል።
7. እግዚአብሄር የእርሱ ለሆኑት ህዝቦቹ ሊያደርግ ያለውን ነገር አህዛብ ተረድተው በእርግጠኛነት እንደዚህ አይነቱን ነገር ሲናገሩ፤ እኛ የእግዚአብሄር ለሆነው ሰዎች በውስጣችን እምነትንና ከዚያም የመነጨ ድፍረትን ሊፈጥርልን ይገባል።

# ጥናት ሰባት አስቴር 7፡1-10 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በቁ 3 ላይ ንግሥት አስቴር ንጉሱን የጠየቀቻቸው ጥያቄዎች አንደኛው የእርሷን ሕይወት እንዲታደግ ሲሆን፤ ሁለተኛው ጥያቄዋ ደግሞ ሕዝቧን እንዲያተርፍላት ነበረ።
2. ንግሥት አስቴር "ሕይወቴን ታደጋት" ብላ የተናገረችበት ምክንያት የህዝቧ ጥያቄ እንደ ራሷ ጥያቄ፣ የህዝቧንም ህይወት እንደ ራሷ ህይወት አድርጋ የመቀበል ጉዳይ እንጂ ይህ ልመናዋ የራሷን ህይወት ማትረፊያ ጥያቄ አይደለም።
3. አስቴር በሥጋ ከአብርሃም ዘር ለተወለዱና ከአንድ ቤተሰብ ለሆኑት አይሁድ ይህንን ያህል መቆርቆር ማሳየት ከቻለች፤ እኛ ደግሞ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ከእግዚአብሄር ቤተሰብ ተወልደን አንድ ቤተሰብ ለሆነው ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ከዚህ በላቀ መንገድ ልንቆረቆር እንደሚገባን ያስተምረናል።
4. በአስ 4፡9-11 ላይ አስቴር ለመጀመሪያው የመርዶኪዎስ ጥያቄ ምን ያህል በራሷ ህይወት ዙሪያ ብቻ እንደመለሰችለት እናያለን፤ ለሁለተኛ ጊዜ መርዶኪዎስ በ4፡12-14 ላይ ግልጽ በሆነ መንገድ ያስተላለፈው መልዕክት ሙሉ ለሙሉ አመለካከቷን እንደቀየረው ከአነጋገሯ መረዳት እንችላለን።
5. መርዶኪዎስ የአስቴርን የመጀመሪያ ምላሽ እንዳለ ተቀብሎ ነገሩን ቢተወው ኖሮ ውጤቱ እንደምናውቀው ላይሆን ይችላል። እግዚአብሄር የመርዶኪዎስን ጽናትና እውነቱን እንዳለ አፍርጦ መናገሩ ለአይሁድ ደህንነት እንዲገኝ የተጠቀመበት ይመስለኛል።
6. በቁ5-7 ላይ እንደምንመለከተው ንጉሱ ጠረክሲስ የቁጣው ንዳድ ሃማን እዚያው ተቀምጦ ለማየት እንኳን ስላልቻለ ወደ አትክልቱ ቦታ ወጣ ብሎ ቁጣውን ማብረድ እንዳስፈለገው ክፍሉ ይነግረናል። ሐማ ምንም ዓይነት መሥዋዕትነት ላልከፈለላት አስቴር ይህንን ያህል ካስቆጣው፤ ኢየሱስ በደሙ ለገዛትና ለሞተላት ሙሽራው ለቤተ ክርስትያን ጠላት ሊያጠፋት ሲመጣ ከዚህ በበለጠ በቁጣው እንደሚገለጥበት አያጠራጥርም።
7. እግዚአብሄር ማድረግ የሚፈልገውን ማናቸውንም ነገር ለማድረግ ረጅም ዓመታት ወይም ብዙ ቀናት እንደማይወስድበትና፤ ማዳን የፈለገውን ለማዳን፣ ማጥፋት ያሰበውንም ለማጥፋት የሚችል ሁሉን ቻይ አምላክ እንደሆነ በግልጽ ያረጋግጥልናል።
8. የእግዚአብሄር ሞገስ በእኛ ላይ እንዳለ እንዳለ እርግጠኞች እንሁን እንጂ፤ ሰዎች እኛ ሳንጠይቃቸው ወይም ሳናስገድዳቸው በራሳቸው አነሳሽነት የሚያስፈልገንን ነገር ለማሟላት እግዚአብሄር ራሱ እንደሚቀሰቅሳቸው ከዚህ ታሪክ መማር እንችላለን።

# ጥናት ስምንት አስቴር 8፡1-17 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሄር ፍርድ የዘገየ መስሎ የሚታይባቸው ወቅቶች ቢኖሩም እንኳን፤ በዚህ ክፍል የምናየው ግን እግዚአብሄር ፈጥኖ እንደሚፈርድና ትዕቢተኞችን እንደሚቃወም ነው።
2. ይህች ሴት በህይወቷ የቆረጠችና ሊመጣ የሚችለውን ማናቸውንም ነገር ማለት ሞትንም ጭምር ለመቀበል ዝግጁ እንደነበረች የምናይ ሲሆን፤ እግዚአብሄር ግን በቸርነቱ ሁኔታውን ቀይሮ ሞት ሳይሆን የጠላትን ንብረት ወራሽ እንደሆነች እናነባለን። ይህ ታሪክ እኛ ለእግዚአብሄር ሥራ እስከሞት ድረስ ስንጨክን፤ እርሱ ደግሞ እኛ ያላየነውን በረከት ሊያጎናጽፈን እንደሚችል ያስተምረናል፡
3. እኔ እንደምረዳው በምዕራፍ ሁለት ውስጥ የሁለቱን ሰዎች ማንነት ገልጾ መናገር ምናልባትም ከንግሥትነት ውድድር ውጭ ሊያስወጣት የሚችል መረጃ ሊሆን ስለሚችል በሚስጢርነት መጠበቅ ነበረበት፤ በምዕራፍ ስምንት ውስጥ ላይ የምናየው ግን ሁሉ ነገር ቦታ ቦታውን የያዘ ስለሆነ የእርሷንም ሆነ የመርዶኪዎስን ማንነት
4. ከዚህ ቀደም በፍርሃት ወደ ንጉሱ መግባት አልችልም ባለችበት ወቅት በመርዶኪዎስ አበረታችነት ገብታ እግዚአብሄር ያደረገውን ድንቅ ነገር በዓይኗ ስለተመለከተች፤ ትናንትና የረዳኝ እግዚአብሄር ዛሬም ይረዳኛል የሚለው እውነት በልቧ ውስጥ በመተከሉ ይመስለኛል። (አቤንዔዘር)
5. በእነዚህ ሁለት ቁጥሮች ውስጥ ስንመለከት ንግሥት አስቴር ሁለተኛውን ልመናዋን በንጉስ ዘንድ ለማቅረብ ዋነኛ ምክንያት አድርጋ ያቀረበቻቸው ሁለት ነገሮች፤ በህዝቧ ላይ ሊሆን ያለውን፤ እንዲሁም የቤተሰቧን ጥፋት እያየች ዝም ብላ ማለፍ አለመቻሏ እንደሆነ እናነባለን። እኛም ለእግዚአብሄር ቤተሰቦችና፤ ለእግዚአብሄር ህዝብ ሁሉ የምንቆረቆርና መከራቸው የሚሰማን ልንሆን እንደሚገባን እንማራለን።
6. ንጉሱ የሰጣቸውን ሥልጣን ሳነብ ልክ አንድ ሰው ፊርማውን ቼክ ላይ ፈርሞ የፈለግኸውን ቁጥር ጻፍና ካሽ አድርገው እንደማለት አድርጌ አየዋለሁ። እኔ አግባብ ባለው መንገድ ተጠቅመውበታል እላለሁ ምክንያቱም ቁ11 “ራሳቸውን ከጥቃት እንዲከላከሉና፤ በራሳቸው፣ በሚስቶቻቸውና በልጆቻቸው ላይ አደጋ ሊያደርስ በሚፈልግ ላይ እንጂ ስልጣን አለን ብለው በንጹሐን ላይ ያስተላለፉት ምንም ዓይነት ትዕዛዝ የለም።
7. በአንደኛ ደረጃ የማየው መርዶኪዎስ በሚገርም ሁኔታ በታላቅ ክብር ከፍ ከፍ ማለቱ፤ ሁለተኛው ደግሞ በፍርሃትና በድንጋጤ ተውጦ የነበረው የአይሁድ ሕዝብ በሙሉ፣ ከተማይቱ፣ አውራጃዎቹ ሁሉ በደስታና በሐሴት መሞላታቸው ሲሆን፤ በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ “ከሌሎች አገር ዜጎች ብዙ ሕዝብ አይሁድ ሆኑ” በማለት በሌሎች ላይ ተጽዕኖ መምጣቱን አያለሁ።
8. ከዚህ ክፍል እኔ የምማረው ትልቅ እውነት ቢኖር፤ መርዶኪዎስ ለአስቴር ቸርነትን ሲያደርግ ነገ የሚሆንለትን አስቦ ሳይሆን ከቅን ልብ መልካምን ነገር እንዳደረገ፤ ብድር ከፋይ የሆነው እግዚአብሄር ደግሞ ቀን ቆጥሮ እንደባረከው፤ እኔም ነገ ምን አገኛለሁ ሳልል ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ቸርነት ማድረግ እንደሚኖርብኝ ተምሬአለሁ።

# <u>ጥናት ዘጠኝ አስቴር 9፡1-10፡3 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. የአይሁድ ጠላቶች በአይሁድ ላይ የበላይነት ወይም አሸናፊ እንዳይሆኑ የከለከላቸው አንዱና ዋነኛው ምክንያት ቢኖር የንጉሱ ከአይሁድ ጋራ መወገኑ ነው። ይህንን እውነት ወደ ራሳችን ስናመጣው ጠላታችን ሰይጣን ምንም ያህል ሃይል ቢኖረው ንጉሱ ከእኛ ጋራ ስለሆነ ድሉ የእኛ መሆኑ የታወቀ ነው።
2. ስለ መርዶክዮስ በእነዚህ ክፍሎች ውስጥ የተነገሩት፤ ሀ) በቤተ መንግሥቱ ታዋቂ መሆኑ፤ ለ) ዝናው በየአውራጃው ሁሉ መሰማቱና፤ ሐ) ኀይሉም እየበረታ መሄዱ ናቸው። እነዚህ ሁሉ የመንግሥት ባለሥልጣናት አይሁድን ለመርዳት ምክንያት የሆናቸው የመርዶኪዎስ ፍርሃት እንደነበረ ቁ3 ይነግረናል።
3. “በምርኮው ላይ ግን እጃቸውን አልዘረጉም” የሚለውን ሃሳብ እኔ የምረዳው፤ የገደሏቸውን ሰዎች ቤትና ንብረት አለመዝረፍ ብቻ ሳይሆን በተለይም ምንም ራሳቸውን መከላከል የማይችሉትን ሴቶቻቸውንና ልጆቻቸውን አልነኳቸውም ማለት ይመስለኛል። ይህ የሚያሳየኝ ሕዝቡ ሰው የመግደል ጥማት ያደረበት ሳይሆን ራሳቸውን ለመከላከል እግዚአብሄር ያዘጋጀላቸውን መንገድ በአግባቡ እንደተጠቀሙ ይመስለኛል።
4. ምንም እንኳን ሕዝቡ በዚህ ክፍል ውስጥ ቀኑን የተድላና የደስታ ቀን አድርጎት እንደዋለ ቢነግረንም፤ የመርዶኪዎስ ደብዳቤ ግን ደስታና ምሥጋናው የአንድ ቀን ነገር ብቻ ሳይሆን በየአመቱ የተደረገላቸውን እንዲያስቡ የሚያደርግ ቋሚ በአል ነው ያዘዛቸው። እኛም እግዚአብሄር ያደረገልንን ነገር የምናስበው በዚያች ዕለት ብቻ ሳይሆን፤ ሁልጊዜ እያስታወስን ማመስገን እንደሚኖርብን ያስተምረኛል።
5. መርዶኪዎስና አስቴርን በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስንመለከታቸው ንጉሱ ሙሉ ለሙሉ እንደተማመነባቸውና በተለይም ይህንን ሁኔታ አስመልክቶ ሙሉ እምነቱን የጣለባቸው መሆኑን በግልጽ ማየት ይቻላል።
6. በሜዶንና በፋርስ የነገሥታት መዝገብ ውስጥ የገባ ሰው ነው፤ ከንጉሱ ቀጥሎ ሁለተኛ ሰው ነበረ፤ ከአይሁድ መካከል ቀዳሚውን ሥፍራ የያዘ ሰው ነበረ፤ ለወገኖቹ መልካም ያደረገ ሰው ነበረ፤ ለአይሁድ ደህንነት የቆመ ሰው ነበረ፤ በአብዛኞቹ አይሁዶች ዘንድ እጅግ የተከበረ ሰው ነበረ። ለእኔ ውስጤን የሚነካው የመርዶኪዎስ ባህርይ ለአይሁድ ወይም ለህዝቡ ደህንነት የቆመ ሰው መሆኑ ነው።
7. መርዶኪዎስ በንጉሥ ደጅ መቀመጥ እንጂ ወደ ቤተ መንግሥት የመግባት እድል እንኳን ያልነበረው ሰው ነበረ፤ ሌላው ደግሞ ለሰው ላለመስገድ ቁርጥ ውሳኔ ያደረገ ሰው ነበረ። ራሱ ቆራጥ ሆኖ ሌሎችም ቁርጠኛ ውሳኔ እንዲወስኑ የሚገፋ ሰው ነበረ። እኔ ከዚህ ሰው በዋነኛነት የምማረውና መቀየር የምፈልገው ነገር ስግደቴን ለአምላኬ ብቻ እንጂ ለምንምና ለማንም አለመስገድን እወስዳለሁ።